# የOIR የስደተኛ የአባልነት ስሜት ፕሮጀክት 2023-2025

የስደተኛ ግንኙነቶች ቢሮ (OIR) በበርክሌይ ከሚገኘው ከካሊፎርንያ ዩኒቨርሲቲ Othering & Belonging Institute (OBI) ጋር በትብብር እየሰራ ነው። ፕሮጀክቱ በስደተኛ ማህበረሰቦች የሚገለጹ መረጃዎችን መሰብሰብን ያካትታል።

ላለፉት ከ20 ዓመታት በላይ ጊዜ ውስጥ እንደዚህ አይነት ካውንቲ አቀፍ ፕሮጀክት አልተካሄደም። ይህ ፕሮጀክት ለሚቀጥሉት ብዙ ዓመታት በካውንቲው ውስጥ ስለ ስደተኞች ተሞክሮዎች በተመለከተ የሚኖረንን ግንዛቤ ይቀርጻል። እኛን ስለመቀላቀል እንደሚያስቡ ተስፋ እናደርጋለን። ስለ ፕሮጀክቱ የተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎ የOIR ቡድንን በ immigrant.relations@ceo.sccgov.org ያነጋግሩ።

የዳሰሳ ጥናቱን ለመውሰድ ከታች የተመለከተውን QR ኮድ ይጠቀሙ ወይም ወደሚከተለው ይሂዱ: SCCimmigrantsurvey.com.

## በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

**ይህ ፕሮጀክት የትኞቹን ማህበረሰቦች ያካትታል?**
OIR እና OBI የእንግሊዘኛ፣ ስፓኒሽ፣ ቬትናሚኛ፣ ማንደሪን፣ ካንቶኒስ፣ ታጋሎግ፣ ሂንዲ፣ ፋርስ፣ አረቢኛ፣ የሩሲያ ቋንቋ፣ ኮርያኛ እና አማርኛ ቋንቋዎች ተናጋሪ ስደተኛኞችን በዚህ ፕሮጀክት ላይ እንዲሳተፉ ያነጋግራሉ። በዚህ ሂደት ላይ እንዲያግዙን ከተአማኒ የማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር ቅርርብ እንፈጥራለን።

**ስደተኛ ማህበረሰቦች አስተያየቶቻቸውን እንዴት ማጋራት ይችላሉ?**
በዳሰሳ ጥናት እና የማህበረሰብ ውይይቶች አማካኝነት መረጃ እንሰበስባለን። የዳሰሳ ጥናቱ የተለያዩ የማህበረሰብ ቡድኖች ጋር የመድረስ እድል አለው። ከማህበረሰቡ ጋር መገናኘት ስለ የአባልነት ስሜት፣ የአገልግሎት አቅርቦት እና ሌሎች አስፈላጊ ቅደም ተከተሎች ግንዛቤ ለማግኘት ሊረዳ ይችላል።

**ለዚህ ፕሮጀክት ድጋፍ ማድረጉ ስደተኛ ማህበረሰቦች እና የአካባቢ ድርጅቶችን በምን መልኩ ተጠቃሚ ያደርጋል?**
የአካባቢ ድርጅቶች እና ውሳኔ ሰጪዎች የፕሮጀክቱን ግኝቶች ለፖሊሲ፣ የገንዘብ ድጋፍና የአገልግሎት ቅደም ተከተሎች በመረጃ ግብአትነት ለመጠቀም ይችላሉ። ከፍተኛ የዳሰሳ ጥናቱ የተሳትፎ ደረጃዎች የአከባቢ ድርጅቶችን፣ ጠበቆችና የህዝብ ባለስልጣናትን በካውንቲው ውስጥ የስደተኛ የአባልነት ስሜት እንዲፈጠር ድጋፍ ለማድረግ ጥሩ መረጃ እንዲያገኙ ያስችላቸዋል።

**የዳሰሳ ጥናቱ የሚካሄደው መቼ ነው?**
የዳሰሳ ጥናቱ በመስከረም እና ጥቅምት 2023 ዓ.ም በኦንላይን ይቀርባል።

**የዳሰሳ ጥናቱን እንዴት መውሰድ እችላለሁ?**
የዳሰሳ ጥናቱን በማስፈንጠሪያ ወይም QR ኮድ በኦንላይን መውሰድ የሚቻል ሲሆን ጥናቱ በ12 ቋንቋዎች ይቀርባል። ምንም የወረቀት የዳሰሳ ጥናት አይኖርም።

**የዳሰሳ ጥናቱ የተሳታፊዎችን የግል ሚስጥር የሚጠብቀው እንዴት ነው?**
ተሳታፊዎች ስማቸውን፣ አድራሻቸውን ወይም የስደተኝነት ሁኔታቸውን አይጠየቁም።

**የዳሰሳ ጥናቱ ምን አይነት ጥያቄ ይጠይቃል?**
በዚህ የዳሰሳ ጥናት ውስጥ የሚካተቱ ርዕሰ ጉዳዮች:

- የመኖሪያ ከተማ
- የትውልድ አገር
- ወደ ዩኤስ የተመጣበት ዓመት
- የስራ እና የሥራ ቅጥር ዕድሎች
- በህይወት ውስጥ ያጋጠሙ ተግዳሮቶች ተሞክሮዎች
- በማህበረሰብዎ ውስጥ የሚቀርቡ አገልግሎቶች
- የህግ አገልግሎቶች እንቅፋቶች
- በከፍተኛ ደረጃ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ፍላጎቶች
- የመድልዎ ተሞክሮዎች
- የግል መረጃ ጥያቄዎች